# በካናዳ ዋና ከተማ በኦታዋ እጅግ የተሳካና የደመቀ የተቃውሞ ሰልፍ ተደረገ

ቢሹ ማሞ - ቶሮንቶ፤ ካናዳ

ከቶሮንቶና አካባቢው፣ ከሀሚልተን፣ ከሞንትሪያልና ኦታዋ ከተማ በመጓዝና በመሰባሰብ በመቶዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ረቡዕ ጁን 5 ቀን 2013 ከቀኑ 12፡30 p.m. ጀምሮ በኦታዋ ከተማ ሲቲ ሆል ፊት ለፊት በመነሳት፤ የወያኔ አገዛዝ የሚያካደውን የዘር ማጽዳትና ማጥፋት ወንጀልን፣ በተቃዋሚ ክፍሎች ላይ የሚያደርገውን ግድያና እስራትን፣ የሚፈጽመውን ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ጥሰትን፣ በኦርቶዶክስና እስልምና ሀይማኖቶች ጉዳይ ጣልቃ መግባቱን፣ ሕዝብን በማፈናቀል ለም መሬቶችን ለውጭ ከበርቴዎች መሸጡን፣ ትንታዊና ቅዱስ ገዳማትን በማጥፋት ለእርሻ ማዋሉን በአጠቃላይ አገሪቷን ለከፍተኛ አደጋ ማጋለጡን በመቃወም ታላቅ የተቃውሞ ሰልፍ አካሂደዋል።




ተቀውሞ ሰልፉ ከኦታዋ ሲቲ ሆል ፊት ለፊት ሲነሳ

በርካታ ኢትዮጵያውያን ከቶሮንቶና አጎረባች ከተሞች በአውቶብሶችና በግል መኪኖች ተጉዘው ከሰልፉ መነሻ ስፍራ እንደደረሱ ከኦታዋና አካባቢው እንዲሁም ከሞንትሪያል ተሰባስበው ከሚጠብቋቸው ጋር አንድ ላይ በመሆን የካናዳና የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማዎችን በማውለብለብና የተለያዩ መፈክሮችን በመያዝ በፖሊስ ታጅበው መፈክሮችን በማሰማት በሞቀና በጋለ ስሜት ወደ ፓርላሜንት ሂል ተጉዘዋል። በመንገድ ላይ ለሚተላለፉ ካናዳውያን የሰልፉን ዋና ዓላማ የሚያስረዳ በራሪ ጽሑፍ አሰራጭተዋል።




የተቃውሞ ሰልፉ ወደ ፓርላሜንት ሂል በመጓዝ ላይ

ሰልፉን የሚመሩት የኦርቶዶክስ እምነት አባቶች ከእስልምና እምነት ወኪሎችና ተከታዮች ጋር አንድ ላይ በመሆን ሲሆን፣ ሰልፈኛው በሰንደቅ ዓላማ አሸብርቆ፣ የሴት እህቶቻችን ቁጥር በሚያስደስት ደረጃ ጨምሮና ተጠናክሮ፣ በተለይም የእስልምና እምነት ተከታዮች እህቶቻችን ላይ የጋለ የኢትዮጵያዊነት መንፈስና የትግል ስሜት ሲንጸባረቅ በመታየቱ ከሌሎች ሰልፎች የደመቀና የሚያበረታታ ስሜት የታየበት ነበር።







የተቃውሞ ሰልፈኛው ካሰሟቸው መፈክሮች በጥቂቱ፤

**Stop Ethnic Cleansing in Ethiopia**
**Ethnic Cleansing is a Crime against Humanity**
**Stop Canadian Aid to the Ethiopian Dictatorship**
**Canada Should Condemn Religious interference in Ethiopia**
**Release all Political Prisoners Now**
**Canada Should Demand the Immediate Release of all Journalists**
**Stop Financing Tyranny in Ethiopia**
**Stop Financing a Police State in Ethiopia**
**Ethiopian Muslims are not Terrorists**
**Canada Say: No Democracy, No Money**
**Stop Selling Farm land to the Saudis and the Chinese.**
**Canada Must Act now against the Ethiopian Dictatorship**
**We Condemn Ethnic Cleansing in Ethiopia**

ድምጻችን ይሰማ!

እኔም አቡበከር ነኝ!

የዋልድባ ገዳም ለእርሻ መዋሉን እንቃወማለን!

የአርሶ አደሩ መሬት ለውጭ ከበርቴዎች መሸጡን እንቃወማለን!

አርሶ አደሩ ከእርሻው መፈናቀሉ ይቁም!

ከኢትዮጵያ ህዝብ ጎን እንቆማለን!

እና ሌሎችም መፈክሮች ነበሩ

ከፓርላሜንት ሂል ፊት ለፊት ሰልፈኛው ድምጹን ካሰማ በሁዋላ በፕሮግራሙ መሰረት የመጀመሪያው ተናጋሪ ሊቀ ካህናት ምሳሌ እንግዳ ለሰልፈኛው ባሰሙት ንግግር ኢትዮጵያ የብዙ ሺህ ዘመን ታሪክ ያላት ሁለቱ ታላላቅ ሀይማኖቶች ተከባብረውና ተቻችለው ጎን ለጎን አብረው የኖሩና ችግርም ሲፈጠር ተመካክረው መፍትሄ የሚፈልጉ መሆናቸውን፤ ወደፊትም በሰላም መኖራቸው እንደሚቀጥል በመጥቀስ የዛሬው አገዛዝ በሀይማኖት በዘርና በቋንቋ ሊከፋፍለን ሲሞክር መፍቀድ እንደሌለብን፤ ለመብታችን ለአገራችን ደህንነት እጅ ለእጅ ተያይዘን መጓዝ እንዳለብን ሰፋ አድርገው ተናግረዋል።



ሊቀ ካህናት ምሳሌ እንግዳ ለሰልፈኛው ንግር ሲያደርጉ



አቶ አቡ ረሺድ ለሰልፈኛው ንግግር ሲያደርጉ

ቀጥሎም አቶ አቡ ረሺድ የእስልምና እምነት ተከታዮችን በመወከል ባደረጉት ንግግር ኢትዮጵያ ማንም የአፍሪካና የአውሮፓ አገሮች የት እንዳሉ ሳይታወቅ ታላቅ አገር እንደነበረች፤ የነቢዩ መሀመድን ታሪክ በመጥቀስና የእስልምና ሀይማኖት ከኦርቶዶክስ እምነት ጋር በአንድ ቤት በአንድ እናት ያደጉ በመሆናቸው እጅግ ተከባበረውና ተፋቅረው የኖሩ በመሆናቸው በኦርቶዶክሱ ላይ ሌላ ሀይማኖት በማምጣት ተቀበሉ እንደተባለው ሁሉ ሙስሊሙም “ይህን የሃይማኖት ክፍል” ተቀበል እየተባለ በመንግስት የሚደረገውን ጣልቃ ገብነት እንደማይቀበሉት፤ መንግስትም በሀይማኖት ጉዳይ እጁን ማስገባቱን በመቃወምና የመረጧቸው መሪዎች እስኪፈቱ ድረስና ሲሞክራሲ እስኪሰፍን ድረስ ድምጻችን ይሰማ በሚለው መፈክር ጸንተው እንደሚታገሉ ገልጸዋል።ትግላችንን በአንድነትና በማስተባበር መቀጠል አለብን ብለዋል።



ሚስተር ፖል ዲወር የተቃዋሚ ፓርቲ የፓርላማ አባል (የኦታዋ አካባቢ የፓርላማ ተወካይና)

ሚስተር ፖል ዲወር የተቃዋሚ ፓርቲ የፓርላማ አባል ለሰልፈኛው ባደረጉት ንግግር በኢትዮጵያ መንግስት እየተፈጸመ ያለው ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ጥሰት እንደሚያሳስባቸው ገልጸዋል። ንግግራቸውንም እንደጨረሱ ስለ ኢትዮጵያዊ ወቅታዊ ሁኔታን የያዘ መረጃ ተሰጥቷቸዋል።




አቶ ይቅር በለኝ ያዘጋጁትን መልእክት በግጥም አሰምተዋል።

ቀጥሎም ለካናዳ ጠቅላይ ሚኒስትር የተዘጋጀውን ደብዳቤ ሊቀ ካህናት ምሳሌ እንግዳ ከሁለት ተወካዮች ጋር በመሆን ወደ ጠ/ሚኒስትሩ ቢሮ በመሄድ አድርሰዋል።

በፓርላሜንት ሂል ፊት ለፊት የእስልምና እና የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ጎን ለጎን በየእምነታቸው ጸሎታቸውን አቅርበዋል።




በመጨረሻም የቶሮንቶ ተወካይና የኦታዋ ተወካዮች ለሰልፈኛው ያዘጋጁትን ንግር በጹሑፍ ካሰሙ በሁዋላ የሰልፉን ተካፋዮች አመስግነው ፕሮግራሙ ተጠናቋል።